## የት ሄደ ዘንድሮ ፍርሃተ እግዚአብሔር!

የት ሄደ ዘንድሮ ፍርሃተ እግዚአብሔር?
በኢትዮጵያ ክልል፣ አህጉርና  አገር።
ኸረ አትሳለቁ አልሆነም ብላችሁ፤
ወንድሙን ወንድሙ ሲገድል፣
በራፍ ቆጭ ብላችሁ
በቆጡም በምስኮት እያዩ ዓይኖቻችሁ።
የት ሄደ ዘንድሮ ፍርሃተ እግዚአብሔር?
በኢትዮጵያ ክልል፣ አህጉርና  አገር።
ማነው አሰላፊው ማነው አጨብጫቢው፤
ደግ አረጉ እያለ ወሬ የሚነዛው?
እጅ እግርን ቆራርጦ በአቆማዳ አሽጎ
የወንድሙን ሥጋ ለናቱ ሊሰጣት፣
ቅፍፍ ሳይለው መስሎት ከሉካንዳ ለሷ እንደገዛላት።
እንዲት አዋቂ ጠፋ በእትዮጵያ መሪት?
አውግዞም የሚነቅፍ ይህን መጥፎ ድርጊት።
ጭራሹን አቁሙ በማለት አዋጅ የሚምታም፤
ፍጹም እንደሆነ የሚጸየፍና ከአራዊት የባሰም።
እጅግ የሚደንቅና የሚያሳፍረውም፣
አንድ ሽህም ሆነ ወይም አንድ ጳጳስ የሚናገር እውነት፤
መጥፍቱ እኮነው በእትዮጵያ መሪት።
በጎሣ ተደራጅቶ ክርስቲናኖችን ከሚያጠፋ፤
ደግሞስ ከሚገድል በእምነትና በጎሣ፣
እንድዲትስ ተው አይሆንም የሚል አባውራ ጠፋ።
ሐራም ነው! ብሎ ወይንም ነውር ነው እያለ ጩሆ የሚቆጣ፤
አላህ አይወደውምም በማለት
በየፍርድ ቤቱ ያን ድርጊት ለመግታት ፈርዶ የሚቀጣ።
ኸረ ባላህ በሉ ወይንም በሱስ
ስታዩ ቀን ከሊት ጭራሽ የሚያጸይፍ፤
ቆራርጦ የሚገል እርጉዝ ሆነ ሌጣም በኪበሌውች ሰይፍ፤
የት ሄደ ዘንድሮ ፍርሃተ እግዚአብሔር?
በኢትዮጵያ ክልል፣ አህጉርና አገር።
አገሪ ኢትዮጵያ ተራራው አይደለም
ሽለቆም አይደለም የቋንቋወች ብዛትም አይደለም
አንችን የቀረጹሽ፣
የሕዝብሽ ቃልኪዳን ነበር ያከበረሽ፤
አረንጓዲ፣ ብጫ፣ ቀይ ነው ባንዲራሽ፤
ከዘመናት በፊት ያንች ክብር
ክብሬ ነው ብለው ያወጇልሽ።
አንችዬ ኢትዮጵያ ከቶ ምን አደረግሽ፣
አውሮፓ፣ አሜሪካ፣ ተምሪያለሁ ባዩ፣
ደግሞ እንደልብሱ አእምሮውን ለውጦ፤
ኢትዮጵያን በመጥላት  መንደሪ አገሪ ነው
እያለ ያውጇል ተቀምጦ እንጦጦ።

አላስተውል አለ ያረገውን ጥፋት፤
እኔ ካልገዛሁሽ ሁኝ እንደሱማሌ እያለ ያጎራል
ሕዝብሽን በማድማት አመሉ ሆኖበት።
            የት ሄደ ዘንድሮ ፍርሃተ እግዚአብሔር?
            በኢትዮጵያ ክልል፣ አህጉርና አገር።
ኧረ ባላህ በሉ ወይንም በየሱስ፤
ዓይናችን እያዩ እንዴት ጭጭ እንበል፣
ወንድም ወንድሙን ገድሎ እስክጨርስ።
ኡ! ኡ! የሕዝብ ያለህ ተው ተመከሩ፤
ወንድምን፣ እህትን በቁም ልትቀብሯቸው የምትቆፍሩ።
ዓለም መሰከረ በዚያ በሻሸመኔ ድርጊቱ ሲፈጸም፣
ተው ተመከሩ ቀን ሳይመሽባችሁ
ደግሞም አስተውሉ ይኸ ነው እውነቱ፤
እሳት እንጨትን ሲበላ አመድ ነው ውጤቱ።
ስሙ እንንተ ሞኞች ሰውን ጨርሳችሁ አገር ብትፈታም፤
የኋላ የኋላ መተላለቅ እኮ ይተርፋል ለናንተም።
ይለቀስ አልነበር ሲሞቱም አዛውንት፣
ይፈጸምም ነበር ቀብራቸው በአክብሮት፣
እስኪ አስቡበት ለናንተ አባቶችም
እንዴት ይደረጋል አገር የጠፍ ለት፤
ያነ እንደሚሆን ምሥክር አለ እኮ የሱማሌ ይዞት።
            የት ሄደ ዘንድሮ ፍርሃተ እግዚአብሔር?
            በኢትዮጵያ ክልል፣ አህጉርና አገር።
ኧረ ተው አውግዙ ሐራምም ነው በሉ፣
ሐገርን ለመቅበር ሰውን በመጨርስ ከሆነ ግባቸው፤
ጠፉ ወይ አባውራ አረ ተው አይበጅም ብሎ የምያስተምራቸው።
በኮበሌ ምሪት አገርን ይናዳል!
ወይንስ አህያ እንዲህ አለ እንደሚባል፤
ማለታቸው ነው ወይ፣ “እኔ ከሞትሁ ሰርዶ አይባቀል።”
ኧረ ባላህ በሉ ወይንም በየሱስ፤
እንዴት በኮበሌ ሰው ሁሉ ይታመስ!!!
አገሪ ኢትዮጵያ ምኑን መርዝ በላሽው፤
ለቀብር ዳርጎሻል ከሆድሽ የወጣው።
            የት ሄደ ዘንድሮ ፍርሃተ እግዚአብሔር?
            በኢትዮጵያ ክልል፣ አህጉርና አገር።
            ኧረ ባላህ በሉ ወይንም በየሱስ፤
            እንዴት በኮበሌ ሰው ሁሉ ይታመስ!!!

© ለምለም ፀጋው፣ ሐምሌ 1, 2012